# ህወሓት/ወያነና የትግራይ ሕዝብ

**(ክፍል ሁለት)** ከነቢዩ ያሬድ

ባለፈው ያቀረብኩት ክፍል 1 ጽሑፌ "ተሓህት/ወያነ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭና ጥቅም አስከባሪ ነውን? የትግራይ ሕዝብ ከመሰረቱ ጀምሮ የተሓህት/ወያነን ዓላማ ደግፎና በእርሱ ተመርቶ ተንቀሳቅሷልን?" የሚሉትን ጥያቄዎች ነበር የተመለከተው። የተጠቀሱትን ጥያቄዎች ስንወያይ ያቀረብኳቸው ታሪካዊ ማሳያዎች የሚያደርሱን ሀቅም የትግራይ ሕዝብ ተሓህት/ወያነን ይቃወምና ይፋለመውም እንደነበር፣ አሁንም እግር ከወርች ታፍኖ እንዳለ በመሆኑ "እንዴት ሆኖ ታዲያ ተሓህት/ወያነ አሸነፈ?" በማለት አንባቢያንን መሰናበቴ ይታወሳል። ከዚያው ልቀጥል።

የትግራይ ሕዝብ ተሓህት/ወያነን ይቃወም ነበር እንጂ አልደገፈም ሲባል ይህንን በተመለከተ ተዘውትረው የሚደመጡና የሚነሱ ጥያቄዎች አሉ። ሕዝቡ ተሓህትን የሚቃወም ከነበረ እንዴት ሆኖ ታዲያ ተሓህት/ወያነ አሸነፈ? ለምንስ አይቃወመውም ወይም ሲቃወመው አይታይም? በማንስ ተደግፎ ነው አገሪቱን አምቆ እየገዛ ያለው? የሚሉትና የመሳሰሉት። አንዳንድ ወገኖች የፋሺስቱ መንደርተኛ ድርጅት የተሓህት/ወያነንና የትግራይ ሕዝብን አንድነት ለማስረገጥ እንደ መከራከሪያ የሚያቀርቡት ነጥብ ታዲያ ለምን አይታገላቸውም የሚል ነው። ግራ የሚያጋባው ግን ለምን ይህ ጥያቄ ሌላውን የአገራችንን ሕዝብንም አስመልክቶ እንደማይቀርብ ነው። እንኳንስ በልጅ ፣ በቤተ-ሰብ፣ በሥራ ቦታ፣ በአካባቢ ሚሊሻ፣ በካድሬ፣ በ"ሕዝባዊ" ማኅበራት፣ ... የስለላ ድር ተጠፍንጐና በግል ንብረትነት ደረጃ ታግቶ ያለው የትግራይ ሕዝብ ቀርቶ በንጽጽር ሲታይ፤ በፈራ ተባም ቢሆን፤ ድምጹ የሚያሰማለት ወገን ያለው የሌሎች ክፍለ-ሀገራት ሕዝብም ቢሆን በእመቃው ብዛት ምክንያት ሆኖ መገኘት የሚገባውን ሆኖ ሲገኝ አይታይም።

ያም ተባለ ይህ የትግራይ ሕዝብ በርግጥ ተሓህት/ወያነን ይቃወም ነበር፤ ተዋግቶታልም። ይህ ማለት ግን ድርጅቱ አመጹን ሲጀምርም ሆነ በቀጠሉት ዓመታት በትግራይ ውስጥ ወይም የትግራይ ተወላጅ የሆነ ምንም ደጋፊ አልነበረውም ወይም የለውም ማለት አይደለም። ነበረው። ለምሳሌ፥ ከጅምሩ ጀምሮ ጥላው ባጠላበት አካባቢ ነዋሪ በነበረውና በተለያየ ምክንያት ከትግራይ ውጭ ይኖር በነበረው የክፍለ ሀገሩ ተወላጅ ውስጥ በጭፍን የትግራዋይነት ስሜት የተመሠረተ ውሱን ድጋፍ ነበረው። ጠባብ አመለካከት ያጠቃቸው፣ በአማራው ጐሳ ጥላቻ የሰከሩ (የመጀመሪያው "ውፈር ተበገስ ተጋዳልይ ትግራይ፣ ሲሕብካ በሎ ነዞ ዓሻ አምሓራይ"፤ ዘፈናቸውን ልብ ይለዋል። ትርጉሙ "ዝመት ተነስ የትግራይ ታጋይ፣ ሳብ አርገህ ግጨው ያንን ጅል አማራ" ማለት ነው)፣ በትግራይ ኪሳራ ኤርትራን

የማስገንጠል አጀንዳ ያነገቡ፣ የፊውዳላዊው ሥርዓት ተንኮታኩቶ የአባቶቻቸው መሬት በመወረሱ ያኰረፉ ቀለም ቀመሶችና ጭፍን ተከታዮቻቸው፣ ወዘተ … የዚሁ ድርጅት የድጋፍ እምብርት ነበሩ። በዚህ ጽሑፍ ለማመልከት የተፈለገው አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ፤ በተለይ ደግሞ ከምዕራብ እና ከፊል መሃል ትግራይ ውጭ የነበረው የክፍለ-ሀገሩ ሕዝብ ተሓህት/ወያነን የማይደግፍ እንደነበረ ነው። ያም ሆነ ይህ ግን የትግራይ ሕዝብ ፀረ-ተሓህት/ወያነ አቋም በረጅም ሂደት ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች እየተዳከመ መጥቷል። ከምክንያቶቹ ጥቂቱን መጥቀስ አስፈላጊ ነው።

ለ14 ዓመታት ያህል ተሓህት ወያነ ትግራይን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ሳይችል ቆይቷል። በተለይ እስከ 1976/77 ድረስ እንደሽምቅ ተዋጊነቱ ድንገተኛ አደጋ እየጣለ በአንዳንድ ከተሞች በነበሩ ወታደራዊ ሠፈሮችና በመጓጓዣ አጀባ ወቅት ጉዳት እያደረሰ ሲያፈገፍግ የነበረ ቢሆንም አብዛኛው እንቅስቃሴው በከፊል መሃልና በምዕራባዊው ክፍል ተገድቦ ቆይቷል። በሰሜን፣ ምስራቅ፣ ደቡብና ከፊል መሃል ትግራይ የነበረው ተቀባይነትም የጐላ ሳይሆን ቆይቷል፤ በፋሺስታዊ ተግባሩ ከመፈራቱ በቀር። ከ1976/77 ዓ.ም. ጀምሮ ግን የአገርና የሕዝብ ደኅንነት መ/ቤት በፈጸመው አሳዝኘ በክህደትም ይሁን የሙያ ብቃቱን ደካማነት ባጋለጠ ስህተት ወይም፤ በሌላ የተሻለ አገላለጽ፤ በአገር አንድነትና ደኅንነት ላይ የፈጸመው ወንጀል ምክንያት ሁኔታው በፍጥነት መቀየር ጀመረ። እጅግ በርካታ የክፍለ-ሀገሩ ተወላጆች ባልዋሉበትና ባልሆኑት የተገንጣይ ቡድኖች አባላት ሆነው ተገኙ በማለት ለእስራት፣ ለግርፋት፣ ለአካል መጉደልና ለሞት ዳረጋቸው። የእነዚህ የአንድነት ኃይሉ ግምባር ቀደም ተዋናዮች ቤተሰብ ፈረሰ፤ ልጆቻቸውና የሚጦሩት ሁሉ ለችጋር ተዳርገ፤ ለመሳቀቅና አንገት ለመድፋት ተገደደ። እነዚህ ሰዎች በትግራይ ውስጥ ከክፍለ-ሀገር እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ በመንግሥትና በማኅበራት መዋቅር ውስጥ ተመድበውና ተመርጠው ሲሰሩ የነበሩ ጉልህና ጽኑ ፀረ-ተሓህት አቋም የነበራቸው ሰዎች ናቸው። በትጥቅ ትግሉም ጭምር ተሓህት/ወያነን እያሳደዱ ሲቀጡና መግቢያ መውጫ ሲያሳጡ የነበሩ ጽኑ ኢትዮጵያዊ አቋም የነበራቸው ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ናቸው እንግዲህ በተሓህት/ወያነ ሥውር ደባና በዋናነት ግን በአገርና የሕዝብ ደኅንነት ጥበቃ መሥርያ-ቤቱ የሀገር ክህደትም ይሁን ንዝህላልነትና ብቃት ማነስ "የወያነ አባለት" ተሰኝተው ከውጭ አገር ሳይቀር በወረንጦ ተለቅመው ለተባለው እስርና መከራ የተዳረጉት። ይህንን ጉዳይ አቶ ገብሩ አሥራትም በመጽሓፋቸው ጠቅሰዉታል (ገብሩ፣ 2006፣ ገፅ 159-161)። ከነዚህ ሰዎች መካከል ጥቂቱ በተለያየ ምክንያት ሕይወታቸውን በእስር-ቤት አጥተዋል። ገሚሱ በጀ/ል ታሪኩ ላይኔ የትግራይ ጦር አዛዥነት ወቅት ተሓህት/ወያነ የመቀሌ ወኅኒ-ቤትን በወረረበት ጊዜ አስፈትቶ ወስዷቸው ከፊሉ ድርጅቱን ሲቀላቀሉ ከፊሉ ደግሞ በሱዳን በኩል ወደ ምዕራብ አገራትና ጥቂቱ ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል። አብዛኞዎቹ ደግሞ ከ1976 ዓ.ም. ጀምሮ በእስር ቆይተው ወያነ የተረከባቸው ሲሆን ከፊሉን ፈቶ ከፊሉን ደግሞ አባሎቹ ናችሁ በተባሉለት በወያነ ዘመንም እስራታቸው ቀጥሎ እስካሁንም ድረስ ያልተፈቱ አሉ፤ ጥቂቱ ደግሞ በግርግሩ አምልጠው

በስደት ይኖራሉ። ይህ መከራ ከደረሰባቸው ሰዎች ውስጥ የተወሰኑት በተሓህት/ወያነ ውስጥ ታቅፈው ለበርካታ ዓመታት የሠሩና እየሠሩ ያሉ ሲሆን፤ ጥቂቶቹ በደረሰባቸው የኀሊና ቁስል በበቀል ስሜት ተነሳስተው ከልብና በፈቃደኝነት ያገለገሉትን የደርግን ሥርዓት "ትግራዮችን ለማጥፋት የተነሳ" ብለው እስከ መክሰስ ድረስ ሄደዋል።

በኰ/ል ተስፋዬ ወልደ-ሥላሴ የአገርና የሕዝብ ደኅንነት ሠራዊት በተሓህት/ወያነ አባልነት ተወንጅለው በአፈሳ ለእስር፣ ለስየልና ለሞት ከተዳረጉት የትግራይ ተወላጆች መካከል፣ የራሳቸው ድርጅት ተንኰል ጠልፎ የጣላቸው በጣት የሚቆጠሩ የወያነ አባላት የነበሩ ቢሆንም አብላጫዎቹ ግን ለወያነ ህልውና አደጋ የጋረጡ ፀረ-ወያነ ታጋዮች ነበሩ። በጣም የሚገርመው በአገር ጉዳይ ቀርቶ በራሳቸው ህይወትም የረባ ዓላማ ያልነበራቸውም አብረው መታፈሳቸው ነው። ከእነዚህ በወቅቱ ወያነ ተብለው በኰ/ል ተስፋዬ የጅብ ሠራዊት የታፈሱ ዜጎች መካከል አብዛኛዎቹ በወያነ ዘመንም በፀረ-ትግራዋይነት ለበርካታ ዓመታት ታስረው የተፈቱና በእስር በመማቀቅ ላይ ያሉም ይገኙባቸውል። ዕድሉ የገጠማቸው ደግሞ ለማምለጥ በቅተው ኑሮኣቸውን በስደት ዓለም እየገፉ ናቸው። የተሓት/ወያነን ፀረ ኢትዮጵያ አቋም እንደግፍም ያሉና ምንም ፖለቲካዊ ተሳትፎ የሌላቸው፣ የሌሎች ኅብረብሄር እና አፍቃሪ የኢትዮጵያ አንድነት የፖለቲካ ድርጅቶች አባላት የሆኑ የትግራይ ተወላጆች አይደሉም፣ በኢሠፓ መንግሥትም ውስጥ ፖለቲካዊ ተሳትፎ የነበራቸው እንኳ ተገድለዋል፣ ተሠቃይተዋል፣ ከትግል ታግተዋል። በወያነ ተከል የመንግሥት አካላት። ባለኝ ትንሽ ቆየት ያለ መረጃ መሠረት ከነዚህ በሺዎች ከሚቆጠሩት ግፉአን መካከል ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ማየት ይቻላል።

- አቶ በላይ በርሄ (በቅደም ተከተል፥ የተምቤን አውራጃ የሕዝብ ድርጅት ኃላፊ፣ የትግራይ ክፍለ-ሀገር የሕዝብ ድርጅት ኃላፊ፣ ሲታሰር የጎንደር ክፍለ-ሀገር የኢሠፓአኰ ሥራ-አስፈጻሚ ኰሚቴ አባልና የኅብረት ሥራ ማህበራት ጉዳይ ኃላፊ፤ ታስሮ ደብዛው የጠፋ)፣

- አቶ ኃይለ-ኪሮስ አሰግድ (የግምባር ገድሊ ሓርነት ትግራይ አመራር አባል፣ የራያና አዘቦና የእንደርታ አውራጃዎች አስተዳዳሪ እና የዘንዶ ሠራዊት መስራችና አዛዥ የነበረ፤ በኢሠፓአኰ/ኢሠፓ ዘመን ለስድስት ዓመታት ያህል ታስሮ የቆየና ተሓህት/ወያነም እስራቱን ቀጥሎበት እስከ ቅርብ ጊዜ በእስር የማቀቀ።)፣

- መምህር ታደሰ ገብረ እግዚአብሔር (መጀመሪያ የየካቲት 66 ፖለቲካ ትምህርት-ቤት አስተዳዳሪ፤ ሲታሰር የኢሠፓኰ ማዕከላዊ ኰሚቴ አባልና የሸዋ ክፍለ-ሀገር/የአዲስ አበባ የርዕዮተ-ዓለም ጉዳይ ኃላፊ፤ ታስሮ ደብዛው የጠፋ)፣

– አቶ ጎሩይ አስገዶም (በቅደም ተከተል የትግራይ ክፍለ-ሀገር ትምህርት ቤቶች ጽህፈት ቤት ምክትል ሥራ-አስኪያጅ፣ የዓጋመ አውራጃ አስተዳዳሪ፣ የትግራይ ክፍለ-ሀገር ተቀዳሚ ምክትል አስተዳዳሪ፤ በቁጥጥር የማዋል ሙከራ ወቅት እጁን አልሰጥም ብሎ ተታኩሶ የሞተ)፣

– አቶ አብራሃ በላቸው (የሽሬ አስተዳዳሪ የነበረ፤ የተሓህት/ወያነ የሌሊት ቅዠት፣ እያሳደደ ይቀጣቸው የነበረ እና በጣም ይፈሩት የነበረ፤ በኢሠፓአኮ/ኢሠፓ ዘመን ለስድስት ዓመታት ያህል ታስሮ የቆየና ተሓህት/ወያነም እስራቱን ቀጥሎበት በእስር እየማቀቀ ያለ። የቅርብ ጊዜ መረጃ የለኝም።)፣

– አቶ ተስፋሁን አወቀ (የዓድዋ አውራጃ የሕዝብ ድርጅት ኃላፊ፤ በኢሠፓአኮ/ኢሠፓ ዘመን ለስድስት ዓመታት ያህል ታስሮ የቆየና ተሓህት/ወያነም እስራቱን ቀጥሎበት በእስር እየማቀቀ ያለ። የቅርብ ጊዜ መረጃ የለኝም።)፣

– አቶ አብረሃ ውበት (የገርዓልታ እና የሳምሬ ወረዳ አስተዳዳሪ፤ በታሰረበት ወቅት አሁን የተረሳኝ የአንድ የትግራይ አውራጃ የኢሠፓአኮ ቁጥጥር ኰሚሽን ሰብሳቢ የነበረ፤ በኢሠፓአኮ/ኢሠፓ ዘመን ለስድስት ዓመታት ያህል ታስሮ የቆየና ተሓህት/ወያነም እስራቱን ቀጥሎበት በእስር እየማቀቀ ያለ። የቅርብ ጊዜ መረጃ የለኝም።)

– መምህር ብርሃኑ ማሞ (በደርግ ዘመን የመቀሌ ከተማ የመጀመሪያ ከንቲባ፤ በኢሠፓአኮ/ኢሠፓ ዘመን ለስድስት ዓመታት ያህል ታስሮ የቆየና ተሓህት/ወያነም እስራቱን ቀጥሎበት እስከ ቅርብ ጊዜ በእስር የማቀቀ። በዚህ ወቅት የደርጉ ቀዳሚ ዘመቻ መምሪያ መቀሌ ሰፍሮ ነበር)፣

– መምህር አሰፋ እሸቱ (በደርግ ዘመን የመቀሌ ከተማ የመጀመሪያ ምክትል ከንቲባ፤ በኢሠፓአኮ/ኢሠፓ ዘመን ለስድስት ዓመታት ያህል ታስሮ የቆየና ተሓህት/ወያነም እስራቱን ቀጥሎበት እስከ ቅርብ ጊዜ በእስር የማቀቀ።)፣

– አቶ ጉግሳ ተኽለ (የሕዝብ ድርጅት ካድሬ፣ ሲታሰር የመናገሻ አውራጃ የኢሠፓአኮ 1ኛ ፀሓፊ)፣

እነዚህ በመቶዎች ከሚቆጠሩት ተሓህት/ወያነን ቀጥ አድርገው ከመከቱትና ድርጅቱ ይፈጥረው የነበረውን ችግርንም ለዘለቄታው ለመፍታት ጥረት ካደረጉት የክፍለ-ሀገሩ ግንባር ቀደም ፀረ-ተሓህት/ወያነ ሰዎች ውስጥ ተቆንጥረው ለአብነት የተገለጹ ናቸው።

ይህን ከፍ ብሎ የተገለፀው በኢሠፓ ሥርዓት ውስጥ ሲያገለግሉ የነበሩትንና የተሓህት/ወያነ ዓላማን ሳይቀበሉ ከፖለቲካው ዓለም ውጭ ሆነው በመንግሥትም ይሁን በግል የሥራ ዓለም ተሰማርተው ይገኙ የነበሩትን ለኢሠፓ መንግሥት የደኅንነት ቢሮ የጥቃት ኢላማ እንዲሆኑ ያበቃ ሴራ ተሓህት/ወያነ

የሰራው ሴራ ነው። ድርጅቱ እነዚህ ሰዎች አባሎቹ እንደነበሩ የሚያስመስል መረጃ የኢሠፓ መንግሥት የደኅንነት ቢሮ ጆሮ ዘንድ እንዲደርስ በማድረጉ ነው የጅምላ እስሩ የተፈፀመው። ይህ ዕውነታ ከያኔ ጀምሮ ሲነገር የኖረና በስተመጨረሻም ኢሠፓ ራሱም ነቅቶበት ያቆመው አሳዛኝ ተግባር ሲሆን አሁን አቶ ገብሩ በጽሑፋቸው አረጋግጠዉታል።

ይህ ተግባር ለተሓህት/ወያነ የመንግሥት ሥልጣን መቆጣጠርና ኤርትራን የማስገንጠል ድርጊት በር የከፈተ አስዛኝ ስህተት/ወንጀል ሲፈፀም ክፍለ-ሀገሩ በነሻለቃ ሙሉጌታ ሓጐስ (የኢሠፓኣኮ/ኢሠፓ ፲ኛ ፀሓፊ)፣ ጀነራል ከፈለኝ ይብዛ (የክፍለ-ሀገሩና የጦሩ የበላይ አስተዳዳሪ)፣ ኮ/ል ፈቃደ ዋኬኒ (የክፍለ-ሀገሩ ዋና አስተዳዳሪ)፣ ጀነራል ታሪኩ ላይኔ (የትግራይ ዕዝ አዛዥ)፣ ሻለቃ ደስታ መሸሻ (የክፍለ-ሀገሩ ምክትል አስተዳዳሪ)፣ አቶ አምባቸው ደምሴ (የክፍለ-ሀገሩ የኢሠፓኣኮ/ኢሠፓ የሥራ-አስፈጻሚ ኰሚቴ አባልና የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ)፣ አቶ ሳሙኤል ሃብቴ (አቶ አምባቸው ደምሴን ተክቶ የኢሠፓኣኮ/ኢሠፓ የሥራ-አስፈጻሚ ኰሚቴ አባልና የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ)፣ አቶ አፈ-ወርቅ (የክፍለ-ሀገሩ የኢሠፓኣኮ/ኢሠፓ የሥራ-አስፈጻሚ ኰሚቴ አባልና የርዕዮተ-ዓለም ኃላፊ)፣ ሻለቃ ሰሙ-ንጉስ (የክፍለ-ሀገሩ የኢሠፓኣኮ/ኢሠፓ የሥራ-አስፈጻሚ ኰሚቴ አባልና የቁጥጥር ኰሚቴ ሰብሳቢ)፣ ኰ/ል ገብረመድህን (የክፍለ-ሀገሩ ፖሊስ አዛዥ፣ በኋላ በጀነራል ማዕርግ የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ [?])፣ አቶ ውብሸት (የክፍለ-ሀገሩ የሕዝብ ደህንነት መ/ቤት ኃላፊ) ወዘተ… ይተዳደር ነበር።

እነዚህ ባለሥልጣኖች ተሓህት/ወያነ በትግራይ ውስጥ የበላይነት ለማግኘት ስለቻለበት ሁኔታ ተጠያቂነት ያላቸው ሰዎች ናቸው። ዋነኛ ተጠያቂዎቹ ግን ሻለቃ ሙሉጌታ ሓጐስ፣ ሜ/ጀነራል (?) ከፈለኝ ይብዛ፣ ጀነራል ታሪኩ ላይኔ፣ አቶ ውብሸት () እና ማዕርጋቸውና ሥማቸው የተዘነጋኝ የትግራይ ወታደራዊ ዕዝ የፖለቲካና የወታደራዊ ደኅንነት ኃላፊዎች ናቸው። በዋናነት የእነዚህ ሰዎች አደራን ያለመወጣት ተግባር ነው ኢትዮጵያ አሁን ለደረሰችበት መታመስ በር የከፈተው። በተለይ ሻለቃ ሙሉጌታ ሓጐስ፣ ሜ/ጀነራል (?) ከፈለኝ ይብዛ፣ አቶ ሳሙኤል ሀብቴ፣ ብ/ጀነራል ታሪኩ ላይኔ፣ አቶ ውብሸት የትግራይ ሕዝብን የትግል ስሜት ያላሸቁ፤ የአንድነት ታጋዮችን ያዳከሙና አብዛኛው ክፍለ-ሀገሩ በሙስና ተግባር እንዲዘፈቅ ምክንያት የሆኑ አደራ-በሎች ናቸው። የእነዚህ ሰዎችና መሰሎቻቸው በሥልጣን መማገጥና በግል ጥቅም ማሳደድ ላይ አትኩረው መደበኛ ዕለታዊ የስምንት ሰዓት የሥራ ኃላፊነታቸውን ያለመወጣት ተግባር ነው ኢትዮጵያ አሁን ለደረሰችበት መታመስ በር የከፈተው። የእነዚህ ሰዎች አደራ-በይነትና የፈጠሩት ሁለንተናዊ ንቅዘት ለተሓህት/ወያነ አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ መድረስ በር የከፈተ ግዙፍ የአገር ክዳት ስለሆነ በሚገባ ሊገለጽ የሚገባው የአገሪቱ የፈተና ወቅቶች ታሪክ አካል ነው። ወደፊት ተነጥሎ ሰፋ ባለ መልኩ ይታያል።

ሌላኛው እስካሁን ድረስ ምስጢሩ በቅጡ ያልተገለጠው ሕዝቡን ያስቆጣ ተግባር በሓውዜን ላይ የተደረገው የአየር ድብደባ ነው። በዚህ ድብደባ እጅግ በርካታ የከተማውና የአካባቢው ነዋሪ የሆኑ ሰላማዊ ወገኖቻችን በአሰቃቂና አሳዛኝ ሁኔታ ሕይወታቸውን አጥተዋል። ድብደባው የተካሄደው በብርጌዶች የሚቆጠር የተሓህት/ወያነ ጦር በከተማው ሰፍሮ መቀሌን ለማጥቃት ዝግጅት እያደረገ ነው የሚል መርጃ በክቶ ለነበረው የኢሠፓ መንግሥት የደህንነት መሥሪያ-ቤት በመድረሱ ነው። ይህንን አቶ ገብሩና ሌሎቹም የወያነ መሪዎች አሌ ያሉት ቢሆንም የዓጋመና የኽልተ-አውላዕሎ ሕዝብ ቁጣ ለመቀስቀስ ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ሴራ ነው። ይህ ተግባር እንደ ብዙ ሌሎች ነገሮች የስብሓት/መለስ ቡድን ከሌሎቹ የድርጅቱ የአመራር አባላት ጀርባ የፈፀመው ሊሆን ቢችልም ዕውነቱ ግን ይኸው ነው።

ልቦናቸውን ጨፍነው አገዛዙን የሚደግፉ ደካሞችና ጠባብ ጐሰኞች ይህንን ተሓህት/ወያነ የፈጸመውን በርካታ የክፍለ-ሀገሩ ልጆችን ለእስራት፣ ለአስቃቂ ግርፋት፣ ለአካል መጉደልና ለሞት የዳረገበትን አረመኔያዊ ደባም ሆነ ሌላው ሁሉ የሕዝብንና የአገርን ደኅንነትና ጥቅምን የጐዳ ተግባር መፈጸሙ "ለትግሉ መጐልበት ጠቃሚ ስለነበረ ተግቢ ነው" የሚል **ነፈዝ** መከላከያ ያቀርቡለታል። ለነዚህ ነፈዞች ተሓህት/ወያነ ሙሉእ በኵሌሁ የሆነ ምንም ዓይነት ጥፋት የማይፈፅም ድርጅት ነው። በእነዚህ አዕምሮ-ስውራን እይታ ኤርትራን መገንጠሉና (ኤርትራን የገነጠለው እሱ ነውና) አገሪቱን የባሕር በር አልባ ማድረጉ፣ የአገሪቱ ታሪካዊና መተክላዊ ጠላቶች በሆኑት በግብጽና በሱዳን እና በሶማሊ እየተረዳና ከርነሱ ጋር አብሮ የአገር አንድነትን አደጋ ላይ መጣሉ፣ መሬት እየቆረሰ ለሱዳን መስጠቱ፣ የድርጅቱ አቋም የተፃረሩትንና በድርጅቱም ውስጥ ሆነው ከአመራሩ ጋር ልዩነት ያሳዩትን ማስገደሉና መግደሉ፣ ወዘተ … ሁሉ ተገቢም አስፈላጊም ልክም ነበር፤ ነውም። ሌላው ወገን የሕዝብና የአገር ሉዓላዊነትን ለድርድር ሳያቀርብ ተሓህት/ወያነን ከማይወዱ ኃይሎች ድጋፍና ትብብር ሲጠየቅ ግን አገራዊ ክህደት፣ ፀረ-ሉዓላዊነት፣ አሸባሪነት፣ ወዘተ ወዘተ ነው። ደርግ ወይም ሻዕቢያ የትግራይ ተወላጆችን ያሰረ፣ የገደለ እንደሆነ ዘር ማጥፋት ነው፤ ተሓህት ወያነ ከዚያ በበለጠ ይህንን ያደረገ እንደሆነ ግን ለትግሉ መስመር አስፈላጊ ነው። ወይም ተራ ስህተት ነው። ደርግ እንደ መንግሥት፤ በዋናነት ደግሞ የሕዝብ ደኅንነት መሥሪያ ቤትና በክፍለ-ሀገሩ የነበሩ የሲቭልና ወታደራዊ ባለሥልጣኖች ተጠያቂ ለመሆናቸው አጠያያቂ ባይሆንም ይህንን ሴራ በመዶለቱ ተሓህት/ወያነም ቢያንስ እኩል ተጠያቂ መሆኑን ግን ዘንግተዋል።

ሌላው የተሓህት/ወያነ ደጋፊ ኃይል ደግሞ በጠባብ የጐሳ/መንደር ስሜት የሰከረው ጨለምተኛ ክፍል ነው። መለስ ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ በርካታ የዓድዋ ልጆች "ጄነራል"፣ ሚኒስቴር፣ ቱጃር (ዋልጌውን ሼክ ልብ ይለዋል)፣ ወዘተ ... ስለሆኑ ዓድዋ በመላ፤ እንዲያም ሲል ትግራይ በመላ የሆነ የሚመስላቸው በህልም ዓለም የሚዋዥቁ የዋኅን እና መንፈሰ-ደካሞች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

ሌላው እዚህ ውስጥ የሚመደበው ቡድን ደግሞ ከኤርትራ ተባርረው የመጡ እዚያው ተወልደው ያደጉና ትግራይ ተወልደው ኤርትራ ያደጉ ያቀፈው ነው። ለነዚህ ሰዎች የኢትዮጵያ ታሪክ ከግንቦት 20፣ 1983 ዓ.ም. ነው የሚጀምረው። ስለ ትግራይ የገዘፈ የኢትዮጵያ ታሪክ ባለድርሻነት፣ ከዚያ በፊት የትግራይ ሕዝብ ለኢትዮጵያ አገሩ አንድነትና ህልውና እውን መሆንና መከበር የከፈለው መስዋዕትነትና ያደረገው ገድል ያላቸው እውቀት መሬት የወረደ ነው። እዚያው ተወልደው ያደጉ በመሆናቸው አርቲፊሻል ትግራዋይነት የሚሰማቸውና ትግራይም ሆነች ኢትዮጵያ የስደት መጠጊያ ከመሆን ያለፈ ብዙ ትርጉም የሚሰጣቸው አይደለም።

በርካታ ኤርትራ ውስጥ ሰርተው ሃብት አፍርተውና ከብረው የኖሩ በሻዕቢያ ተዋርደውና ንብረታቸው ተዘርፈው የተባረሩትም የተሓህት/ወያነ ስሜታዊ ደጋፊዎች ናቸው። እነዚህ ወገኖች ጫጉላው አልቆ ተሓህት/ወያነና ሻዕቢያ/ህግደፍ ሲራገጡ ተሓህት/ወያነ በደላቸውን የተበቀለላቸው መስሏቸው በስሜታዊነት ሰክረው አድረዉለታል። የተሓህት/ወያነና ሻዕቢያ መራገጥ የሌላ ጐሳ ተወላጆችም ተሓህት/ወያነ ኢትዮጵያዊ የሆነ መስሏቸው እንዲደናበሩ ያደረጋቸው ሲሆን፤ ራስ አሞኝ "ብልጣ-ብልጦቹ" ደግሞ ሰበብዋን ተጠቅመው ወደ አገዛዙ ጠጋ እንዲሉ ሰበብ ፈጥሮላቸው ግብር ለመስፈር ሲጣደፉ ተስተውለዋል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው የደርግ መንግሥት የፀጥታው ቢሮ ባሳየው የዘቀጠ የሙያ ድክመትና በፈጸመው በጣም አሳዛኝ ክህደት በክፍለ-ሀገሩ ቁልፍ ቦታዎችና በግምባርም ጭምር የነበሩ ፀረ-ተሓህት/ወያነና ሻዕቢያ ባለሥልጣናትና ታጋዮች አፍሶ ዘብጥያ አውርዶ ክፍተት በመፍጠሩ ፀረ-አንድነት አማጽያኑ የፖለቲካና ወታደራዊ ምህዳሩ ያለ ከልካይ እንዳሻቸው እንዲፈነጩበት ዕድል አገኙ። ሕዝቡም ተስፋ መቁረጥ ዳምኖበት ደርግን ያመነና ውኃ የዘገነ ብሎ አረፈው። ከዚህ ውጭ ግን የትግራይ ሕዝብ በመላ ወይም አብላጫው ክፍል የተሓህት/ወያነ ደጋፊና ተከታይ ሆኖ የታየበት ጊዜ አልነበረም። ድርጅቱም ደግሞ የሕዝቡ ጋሻና መከታ አልነበረም። አሁንም፤ እላይ ለማብራራት እንደተሞከረው፤ የሕዝቡን ስትራቴጂያዊ ጥቅሞች እየጐዳ የትግራይ ሕዝብ ጥቅም አስከባሪ ሊሆን አይችልም።

የትግራይ ሕዝብ በነፃነት የኖረና ነፃም ሕዝብ ስለሆነ ነፃ አውጭ አልሻውም፣ አያሻውምም። መብቱና ክብሩ ተጠብቆና በልፅጐ ለመገኘት እንዲችል ግን እንደ 1930ዎቹ አሁንም ለፍትሃዊ ሥርዓት መስፈን ይታገላል። ይህ ግን የብተና ፊተውራሪና የባዕዳን ተልዕኮ ፈጻሚ በሆኑት በተሓህት/ወያነ እና በሻቢያ መሪነት እውን ሊሆን አይችለም። ይህ እውን ሊሆን የሚችለው እነሱን በማስወገድ ወይም እነዚህ ቡድኖች በሆነ ተአምር የያዙት አጥፊ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-አገር ዓላማ ሲተዉ ብቻ ነው።

- ተሓህት/ወያነ ሁሉንም የትግራይ አካባቢዎችንና ተወላጆችንስ በእኩል ዓይን ይመለከታል? የታገለውና የሚታገለውስ ታላቅ ትግራይን ለመመስረት ነው?

የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያዊነትና የአገር ፍቅር ማንኛውም እዚያ ክፍለ-ሀገር የኖረና ተዘዋውሮ ያየ ሰው ሊመሰክረው የሚችል ግልጽ ጉዳይ ነው። ይህንን እንደነ አቶ ተክሌ የሻው የመሳሰሉ በክፍለ-ሀገሩ ቁልፍ ቦታ ላይ ተመድበው የሠሩ ሰዎችም ያዩት ኃቅ በመሆኑ ሊመሰክሩለት ይገባ ዘንድ ኢትዮጵያዊ አደራና ሰብኣዊ ግብረ-ገብነት ግድ ይላቸዋል። ዛሬ ሌላ ጊዜ ላይ ነው ያለነው። በዛሬው ወቅት የትግራይ ሁኔታ በአያሌ ውስብስብ ምክንያቶች ሳቢያ ሌላ መልክ ይዟል። ቢሆንም ግን ስለ ትግራይም ሆነ ስለ ሌላው አካባቢ አስተያየት ሲሰጥ የትላንቱን በትላንት የዛሬውን በዛሬ እየተለካና እየተቀመጠ ነው መሆን ያለበት። የትግራይ ሕዝብ ዛሬ ያለ ጠበቃና እውነተኛ ወኪል ቀርቶ፣ የተሓህት/ወያነ የግል ንብረት እስኪመስል ድረስ በጠባብ መንደርተኛ ነፍጠኞች፣ ባዕድ ነን ባይ ከሃዲዎችና የባንዳ ተተኪዎች ታግቶ መጫወቻ ሆኖ ያለ ሕዝብ ነው። ሌሎች ስለ አካባቢው ምንም ዕውቀት የሌላቸው፤ ወይም በጣም የደከመ የአሉ ተባለ መረጃ ያላቸው፤ ወይም በአገዛዙ ፕሮፓጋንዳ ግዳይ የተጣሉ፤ አለያም ለሆነ ጠባብ ዓላማ ሲሉ እውነታውን መካድ የመረጡ ሕዝቡን ከአገዛዙ ጋር አዳብለው ስለሚመለከቱት አለኝታ አልባነት እየተሰማው የሚኖር ሕዝብ ሆኗል። ከዚህ በላይ ደግሞ አንዳንድ ያልተገሩ ደካማና ለአገዛዙ ያደሩ ፍርፋሪ ለቃሚዎች እምር እያሉ በሚያሰሙት ቀረርቶ ቀረሽ ዛቻ (ሌላ ቃል የተሻለ አይገልጸውም) የበለጠ ጥርጣሬ እንዲያድርበትና 'እኛ ከሌለን አለቀልህ' የሚለውን የፋሺስቱ መንደርተኛ ቡድን አርቲ ቡርቲ ሰበካ ለመቀበል እንዲያቅማማ እየተገደደ ያለ ሕዝብ ነው።

እውነቱ ይነገር ከተባለ ይህ መንደርተኛ ፋሺስታዊ ድርጅት በሥሙ ይነግዳል እንጂ ወኪሉም፣ ነፃ-አውጪውም አይደለም፤ ያደረገለትም ነገር የለም። በርግጥ አገዛዙም ሆነ ደጋፊዎቻቸው ፋብሪካ ተሰራ፣ ቤት ተሰራ፣ ቪላ በቪላ ሆነ፤ በየወረዳው ትምህርት-ቤትና የጤና ተቋምት ፈሉ፣ ወረዳዎቹ በመንገድ ተገናኙ፣ ወዘተ ... ይሉናል። አዎ፤ ግን ማን የሠራው ፋብሪካ፣ ባለቤትነቱ ማን የሆነ? የነማን ቤትና ቪላ? የዘመነኛ ነፍጠኞች፣ የአገዛዙ ሹሞችና የአገዛዙ አጨብጫቢ አረመኔ ከበርቴዎችና የአየር ባየር ሞጭላፎች ቪላና ህንፃ ለሕዝቡ ምኑ ነው? ለነገሩማ መንግሥት የሚባል ነገር'ኮ እንዲህ ዓይነት ተግባራት ሊያከናውን እንጅማ የማን ጕፈሬ ሊያበጥር ነው ሕዝቡ የሚቀጥረው?! የተሓህት/ወያነዎች ይህን ቢያደርጉ ኖሮስ ነን ብለው ከሚቦተሉክት አንፃር ደጋፊዎቻቸው ለምን ይደነቃሉ?! ለመሆኑ ይህ ሁሉ በዚያ ኋላ በቀረ የኢኮኖሚ አቅምም ሳይገደቡ ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩምም ሕዝቡን እያስተባበሩ የፈጸሙት ተግባር እንደሆነ የተሓህት/ወያነ ጀሌዎች ያውቃሉ? በርግጥ ልዑሉ በዘመናቸው ያሠሩት ሁሉ ጠላት እንዳይጠቀምበት በሚል ፈሊጥ ተሓህት አፍርሶና ነቃቅሎ አጥፍቶታል፣ በፈንጅ ደረማምሶታል። ዛሬ ይህ መንደርተኛ ፋሺስት ቡድን ይህንን ትላንት ያወደመውን ቢተካ ምን ይገርማል?

እላይ ቆንጠር ተደርጐ ለመግለጽ እንደተሞከረው የአብላጫው የትግራይ ሕዝብ ዓላማና የፋሺስቱ መንደርተኛ ቡድን ተሓህት/ወያነ ዓላማ ፈጽሞ ተቃራኒ ነው። ለማብራራት እንደተሞከረው የዚህ ፋሺስታዊ ቡድን ዋነኛው የተፅእኖ አካባቢ ምዕራባዊው እና ከፊል መሃል የትግራይ ክፍል ሲሆን በሌላው ክፍል እኩል የሆነ ተቀባይነትና ድጋፍ ለማግኘት ሳይችል እስከ የኢሠፓ ሥርዓት መፈረካከስ ዋዜማ ድረስ ለመቆየት ተገድዷል። በተጨማሪም እላይ ጠቆም እንደተደረገው የድርጅቱ አመራር በአብላጫው በአሽዓ (አክሱም፣ ሽሬ፣ ዓድዋ) ተወላጆችና በኤርትራዊያን የተሞላ ነበር፣ ነውም። ከእነዚህም አብዛኛዎቹ አፍቃሪዬ-ኤርትራ የሆኑ ለኢትዮጵያ አንድነት በጐ አመለካከት ያልነበራቸው (አሁንም የሌላቸው) ስለነበሩ ይህንን ዓላማ ይፃረሩ የነበሩትን እጅግ አብላጫው ከሌሎቹ የትግራይ ክፍሎች የሆኑትን አባሎቻቸውን ገና ከማለዳው በግልጽም በሥውርም አጥፍተዋቸዋል። ይህ ደግሞ በአብዛኛዎቹ የደቡብ፣ ምሥራቅ፣ ሰሜንና ከፊል መሃል ትግራይ ተወላጆች ዘንድ ቅሬታ ፈጥሮ የኖረ በመሆኑ ድርጅቱ በአካባቢው ሚዛን የሚደፋ ተቀባይነት እንዳይኖረው ጋሬጣ ሆኖበት ዘልቋል፤ ምንም እንኳን በተለያዩ ምክንያቶች በተነጻጻሪ አነስተኛ የሆኑት የአካባቢው ተወላጆች ድርጅቱን የተቀላቀሉ ቢሆንም። ምክንያቶቹ በዋናነት የኢኮኖሚ ችግር፣ እላይ እንደተጠቀሰው ዓይነት የደህንነቱ መሥሪያ-ቤት የሠራው ዓይነት ጥፋት፣ በጦርነቱ መራዘም ምክንያት የወደፊት ሕይወት አስመልክቶ ተስፋ መቁረጥ፣ ዛሬም እንደሚታየው የምዕራቡ ዓለም የተሻለ ሕይወት ፍለጋ ወደ ስደት ሲያመሩ ድርጅቱ በሚቆጣጠረው ክልል ሲያልፉ ለጠባብ ብሄረኛ ፕሮፓጋንዳ ተጋልጠው ግዳይ በመሆን፣ ወዘተ ... ናቸው።

የእነዚህ አካባቢዎች ሕዝብ እንደ ምዕራቡ እና ከፊል መሃሉ ድርጅቱን ሙሉ በሙሉ ባለመደገፉ በድርጅቱ ግምባር ቀደም መሪዎች ዘንድ ጥርስ ተንክሶበት ኖሮዋል። የድርጅቱ አመራር በአብዛኛው የምዕራብ ልጆች በመሆናቸው የበለጠ መደጋገፍና ግልጽ አድልዎም ይፈፅሙ ነበር። ለዚህም እንደ የጐላ ምሳሌ መለስ ዜናዊ ከግዳጅ ሲፈረጥጥ የተሰጠው ድርጅቱ በወቅቱ ይከተለው ከነበረው ደንብ ጋር የማይመጣጠን ቅጣት መጥቀስ ይቻላል። እንዲህ ዓይነቱ ተግባር የድርጅቱ አባሎች በሆኑት የሌሎች አካባቢዎች ተወላጆች ዘንድ የፈጠረው ቅሬታ በድርጅቱ ዘንድ ህንፍሽፍሽ በመባል ለሚታወቀው የውስጥ መታመስና ለገሚሶቹም ድርጁትን ጥለው ለመኮብለል ምክንያት እስከ መሆን በቅቷል። ዛሬም ቢሆን ይህ ሁኔታ ቀጥሎ ያለ ሲሆን ይህንን ለመረዳት የድርጅቱ ወታደራዊና የሲቭል መሪዎች የትውልድ አካባቢ መፈተሽ ይበቃል።

ድርጅቱ በውስጠ-ድርጅት ሕይወቱ ብቻ ሳይሆን በአደባባይም በግልጽ የሚታይ አድልዎ እየፈፀመ ይገኛል። አድልዎው ጊዜያዊ ሳይሆን ከምዕራቡ ክፍል ውጭ ያለውን ሕዝብ ማንነት መለያ የሆኑ ጉዳዮችንም እስከነአካቴው ለመቀየር ያለመ ነው።

ሌላኛው እንደ ምሳሌ መመልከት የሚቻለው በቋንቋ ረገድ እየተደረገ ያለው ዘመቻ ነው። በትግራይ ውስጥ የተለያዩ የትግርኛ ዘዬዎች (dialects) አሉ። ዓድዋ፣ አክሱምና ሽሬ አካባቢ የሚነገረው ትግርኛ

አንድ ዓይነት ወይም በጣም ተቀራራቢ ሲሆን፤ የኽልተ-ኣውላዕሎና የዓጋመ አውራጃዎች ደግሞ አንድ ዓይነት ወይም በጣም ተቀራራቢ ነው። የእንደርታና የተምቤን ትግርኛ የተለየ ሲሆን ትንሽ ተቀራራቢነት አለው። የራያ ትግርኛ ደግሞ ራሱን የቻለ ነው። በእርግጥ በኩታ ገጠም አውራጃዎች ወይም አካባቢዎች የሚነገረው ትግርኛ ተቀራራቢነት ሊኖረው ይችላል። የሆነ ሆኖ ዓድዋ፣ አክሱምና ሽሬ አካባቢ የሚነገረው ትግርኛ ራያና እንደርታ ከሚነገረው ትግርኛ ይልቅ አንድ ዓይነት ነው ለማለት በሚያስደፍር ደርጃ ኤርትራ ውስጥ ከሚነገረው ትግርኛ ጋር ይመሳሰላል።

እላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ዛሬም አብላጫው የመንደርተኛው ፋሺስታዊ ቡድን ተሓህት/ወያነ መሪዎች የምዕራቡ ክፍል ተወላጆች፣ የኤርትራ ተወላጆች እና የትውልድ ሃረጋቸው ከዚያው የሚመዘዙ ናቸው፤ እንደነ ዶ/ር አዲስ-ዓለም ባሌማ፣ ወ/ሮ ሮማን ገብረ-ሥላሴ (አቶ መለስ ደንቆሮ ብለው የሰየሙዋቸው መንፈሰ-ስንኩል)፣ … የመሳሰሉ እፍኝ የማይሞሉ ማፈሪያዎች ቢያስኰለኩሉም።

ዛሬ የድርጅቱ መሪዎች ባላቸው የሌሎቹን አካባቢዎች ማንነት የመጥላት፣ የመናቅ፣ የማኰሰስና የማጥፋት ዓላማ መሠረት የሁሉም አካባቢ ልጆች በአስገዳጅ ከኤርትራ ጋር የሚመሳሰለውን የዓድዋ፣ አክሱምና ሽሬ ትግርኛ ዘዬ እንዲማሩ እያደረጉ ነው። ይህንን ደፍረው የሚቃወሙ የእነዚህ አካባቢ ተወላጆች በርክተውና ጐልተው አለመታየታቸው ደግሞ የበለጠ አስዛኝና አሳሳቢ ነው። ነገረ ግርምቢጥ ሆኖ አንዳንድ አወቅን መጠቅን የሚሉ የእነዚህ አካባቢ ተወላጆች ግለሰቦችም በነሱ ብሶ ይህንን ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ ነው የሚታየው። እሩቅ ሳንሄድ የአቶ አበበ ተክለ-ኃይማኖትን (ጆቤ) የአቶ ገብሩ አሥራትን መጽሓፍ የተቹበት ጽሑፍ ላይ የተጠቀሙት የትግርኛ ዓይነት መጥቀስ ይቻላል። አቶ አበበ ተክለ-ኃይማኖት ከርዕሱ አንስቶ የተጠቀሙበት ቋንቋ እራሳቸው የተወለዱበት አካባቢና የአፍመፍቻቸው የሆነውን፤ ያደጉበትን ዓይነት ትግርኛ ሳይሆን የአማቾቻቸው አካባቢ ዘዬን ነው (የአቶ አበበ ተክለ-ኃይማኖት ሚስት ወ/ሮ አስካለ የዓድዋ ተወላጅ መሆናቸው ልብ ይለዋል)። የተሓህት/ወያነ አፈቀላጤዎች ይህንን ማለት መከፋፈልና ዘር-ቆጠራ ነው ብለው ሊመፃደቁ የችላሉ። መልሱ አጭር ነው። እንዲህ ማለት በናንተ ቋንቋ ለመናገር ያህል ሳይሆን ዕውነቱን ለመግለጥ ነው። ሁሉም ባህሉና ቋንቋው ይከበርለት ከተባለ ኽልተ-ኣውላዕሎም፣ ራያና አዘቦም፣ እንደርታም፣ ተምቤንም፣ … የራሱ ቋንቋ ዘዬ፣ ልምድና ወግ፣ ወዘተ… ስላለው አክብሩለት ለማለት ነው።

አንዳንድ የዞረባቸውና ማንነታቸው የሚያሳፍራቸው፣ የእነዚህ ማንነታቸው እንዲከስም እየተደረጉ ያሉት አካባቢዎች ተወላጆችና የትውልድ ሃረጋቸው እንደምንም ከኤርትራ ጋር ለማቆራኘት ፍዳቸውን የሚቆጥሩ እንጭጮች ይህንን ተሓህት/ወያነ የሌሎቹን እየተጫኒ እያስፋፋው ያለውን የኤርትራ መሰል የምዕራብ ትግራይ ልሳን **የውድብ ቋንቋ** በማለት ሊያድበሰብሱትና ሊኳኩሉት ሲዳዳቸው ይታያል። የውድብ (የድርጅት) የሚባል ቋንቋ የለም። እንዲያሸንፍና ሌላውን እንዲያጠፋ እየተደገፈ ያለው ቋንቋ የኤርትራ-መሰሉ የምዕራብ ትግራይ ትግርኛ ነው። የነ አቶ መለስ፣ አቶ ስብሓት ነጋ፣ የአቶ ብርሃኔ

ገብረ-ክርስቶስ፣ የአቶ በረከት ስምዖን፣ የአቶ ሳሞራ የኑስ፣ የአቶ ቴድሮስ ሓጐስ፣ ወዘተ ወላጆች ወይም ከወላጆቻቸው የአንዱ አገር ልሳን ነው። ኃቁ ይህ ነው። የኤርትራው ትግርኛ የበላይነት የማቀዳጀቱ ዘመቻ ተሓህት/ወያነ ብቻ ሳይሆን የአሜሪካ ድምጽ ሬድዮም ሥራ ሆኖ ነው የሚገኘው።

- **እውን የተሓህት/ወያነ ታላቅ ትግራይን ለመመስረት ነው የታገለው?**

ሌላኛው የተሓህት/ወያነ መንደርተኝነት፣ ለምዕራቡ የትግራይ ክፍልና ለኤርትራ የሚያደላና የበለጠ የሚቆረቆር መሆን፣ መላው ትግራይን በዕኩል ዓይን እንደማይመለከት አስረጅ የሆነ አብይ ጉዳይ ሥልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ እንዴት የክፍለ-ሀገሩን ካርታ (Map) እንደለዋወጠው ነው። ይህ ጉዳይ ከተሓህት/ወያነ የትግራይ ነፃ አውጭ ነኝ ባይነት ጋር ተያይዞ የሚነሳ ጉዳይ በመሆኑ፤ አንዳንድ ወገኖችም ከተሳሳተ መነሻ በመንደርደር ድርጅቱ መላ ትግራይን ዕኩል የሚያፈቅርና ታላቅ ትግራይን የመመስረት አጀንዳ ያለው አድርገው ስለሚቆጥሩ በሚገባ ሊብራራ የሚገባ ታላቅ ጥያቄ ነው።


እላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የትግራይ ሕዝብና የተሓህት/ወያነ ዓላማዎች ለየቅል ናቸው። ድርጅቱም የትግራይን ሕዝብ በመላ በእኩልነት ዓይን እንደማይመለከት እላይ ለመግለጽ ተሞክሯል። ተሓህት/ወያነ ለምዕራባዊው ክፍል የሚያደላ፣ ለሚወደው ለሚሳሳለት አካባቢ ጨምሮለትና (ይህ ራያን አይመለከትም፤ የተወሰደበት መሬት ከተጨመረለት ያነሰ ነው።) የሚጠላውንና ቂም የቋጠረበትን ግን ጐምዶ ጐማምዶ ያስቀረውን ትግራይን የመገንጠል አጀንዳው (ከኢትዮጵያ ገንጥሎ ከኤርትራ ጋር ለማዋሃድ) ያልቀየረ፣ የትግራይ ሕዝብ ስትራቴጂያዊ ጥቅሙ የሚያስከብርለትንና በዘመናት መስዋዕትነት የገነባውን ኢትዮጵያዊነቱን የሚገድል ድርጅት እንጂ ለትግራይ ጥቅምና ታላቅነት የሚጥር ድርጅት አይደለም። የተሓህት/ወያነ የትግራይ መውደድና ተቆርቋሪነት የሚገለጸውና እውን የሚሆነው በነባራዊው ዓለም ሳይሆን እውነቱን ማየት በተሳናቸው ተቃዋሚዎችና በያዘው ልቀቀው ዘፈንና በወርቅ ዘር አፍዝዝዝ አደንዝዝ ፕሮፓጋንዳ በታወሩ የዋኀን የክፍለ-ሀገሩ ተወላጆች ምናብ ውስጥ ነው። በነባራዊው ዓለም የምናየው እውነታ ግን የዚህ ተቃራኒ ነው።

በመሠረቱ የተሓህት/ወያነ አመራር የትግራይን ሁሉንም አካባቢዎች እኩል ወይም በተመዛዛኝ ሁኔታ ያልወከለ፣ የክፍለ-ሀገሩን ሕዝብን በእኩል ዓይን የማያይ፣ ከብቅለቱም ጀምሮ በምዕራብ ትግራይ ተወላጆች የተሞላና ለዚያ የሚያደላ ሆኖ የተፈጠረ ስለሆነ ታላቅ ትግራይን የመፍጠር ዓላማ አልነበረውም፤ የለውምም። በርግጥ ግምባር ገድሊ ሓርነት ትግራይ (ግ.ገ.ሓ.ት. = TLF) የተባለው ተሓህት/ወያነ ያጠፋው ድርጅት እንዲህ ዓይነቱን ዓላማ ይዞ ተንቀሳቅሶ የነበረ በመሆኑ የተጫረውን ስሜት ለመሳብ አልሞ ሊሆን በሚችል ምክንያት ተሓህት/ወያነም እንዲያ የመሰለ ግን ጠበብ ያለ ካርታ ይዞ የተወሰነ መንገድ ተጉዟል። እውነተኛው አጀንዳውና ዓላማው ግን ሥልጣን በጨበጠ ጊዜ አሳይቷል። በእርግጥ ተሓህት/ወያነ ገና የቀረው ያልቋጨው ቁልፍ አጀንዳ አለ። ይህም ቢቻል እሱ

የፈጠራትን የአሁንዋን ትግራይ በመላ ካልሆነ ደግሞ ምዕራባዊና ሰሜናዊ ክፍሏን ገንጥሎ ከኤርትራ ጋር የማጠቃለል አጀንዳ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እነ አቶ ስብሓት ነጋ ትግራይና የቀሩት የክፍለ-ሀገሩ ክፍሎች ታሪክና ግንኙነት አስመልክቶና ኤርትራን አስመልክቶ ፍንትው እያደረጉልን ያሉት አመለካከት ልብ ላለው ሰው ይህንን ጠቋሚ ነው። "የራስዋ እያረረባት የሰው ታማስላለች" እንዲሉ ለዜጐችዋ በቂ የትምህርት ተቋማትና ጥራት ያለው ትምህርት ማቅረብ ያልቻለችው ኢትዮጵያ ጠላታችን ነሽ ብለው ጡቷን ለነከስዋትና መገንጠልን መርጠው ለጠነጠንዋት የኤርትራው ክፍል ተወላጆች ሲሆን ጊዜ በርዋን በርግዳ ማምበሽበሽዋ አቶ መለስ የደሰኮሩልንም ሌላ ነገር አይደለም የሚያሳየን። አቶ መለስ ይህንን ሲነግሩን በብሽቅ ቀመር እርር-ድብን በሉ ለማለት ፈልገው ይሁን ወይም እንደ ድል ቆጥረዉት፤ ወይም ለእናታቸው የትውልድ አካባቢ ሰዎች ያላቸው የተለየ ፍቅር ሊያሳዩን ፈልገው ይሁን እምብዛም ሳይገደን ዓላማው ግን በኢትዮጵያዊያን ሃብት ኤርትራን በተማረ የሰው ኃይል (Human Capital) ለማጠናከር መሆኑን ማወቅ ይገባል። ከፍ ሲል ደግሞ ለመጪው የትግራይ-ትግርኚ ምሥረታ ቅድመ ዝግጅት ሊሆን እንደሚችል አለመጠርጠር የአእምሮ ስንኩልነት ነው።

በአጭሩ ተሓህት/ወያነ ታላቅ ትግራይ የመመስረት ዓላማ የለውም። ተሓህት/ወያነ ለኤርትራ ካለው ፍቅር በቀር ይዞት የዘለቀ መሠረታዊ አስተሳሰብ የሌለው፣ ከግራ ጫፍ ወደ ቀኝ ጫፍ የሚንከላወስ፣ በየወንዙ ዳር አቋሙን የሚለዋውጥ የአየር-ባየር ፖለቲካ አራማጅ ስለሆነ እንዲህ ወይም እንዲያ አያደርግም ወይም ያደርጋል ማለት ቀላል ባይሆንም ቢያንስ እስካሁን እንዲህ ዓይነት ዓላማ የለውም። ተሓህት/ወያነ ታላቅ ትግራይን የመመሥረት ዓላማ ቢኖረው ኖሮ ሂሳብ ሳያወራርድ ተሯሩጦ ኤርትራን ባላስገነጠለ፣ በረጅም ዕቅዱና ህልሙ መሠረት ወደፊት ኢትዮጵያ ብትንትኗ ወጥቶ በትናንሽ መንግሥታት ስትተካ ትግራይ ወደ ባሕር ቅርበት እንዳይኖራት በማቀድና (ባሕሩ ያለው በምሥራቅ በኩል ስለሆነ!) በትግርኛ ተናጋሪው ሕዝብና በአፋር ሕዝብ መካከል የግጭት ጥንስስ እንዲሆን በማሰብ የቀድሞዋ ትግራይ ግማሽ ያህል የሆነውን የክፍለ-ሀገሩን ምሥራቃዊ፣ ሰሜናዊ-ምስራቅና ደቡባዊ-ምሥራቅ ክፍልን ቆርጦ ወደ አፋር ክልል ባላካተተ ነበር **(ካርታ ቁ. 4, 5 እና 6 ይመልከቱ)**።

የተሓህት/ወያነ መሪዎች በምሥራቃዊ ትግራይ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ፣ ፍርሃትና ንቀት የተደበላለቀበት ስሜትና አጀንዳ ይዘው ነው የሚጓዙት። የአቶ ስብሓት "እንደርታዎች ትልቅ ዳቦ እንጂ ትልቅ ሰው የላቸውም፣ እንደርታዎች ሙያተኛ ለማኞች ናቸው፣" ዓይነት ብልግና የተመላበት አነጋገር፤ የምዕራቡ ክፍል ተወላጅ የሆኑና የነሱ አሽከሮች እንደሚያላዝኑት እንደርታዎች፣ ዓጋመዎች፣ ራያዎች ምንም አልተዋጉምና የጠላት መሣሪያ ነበሩ፤ "ትግርኛ ዓድዋ ተወለደች፣ አክሱምና ሽሬ አደገች፣ ዓጋመና ተምቤን ታመመች፣ መቐለ ሞታ ራያ ተቀበረች፤" ወዘተ ... የመሳሰሉ ብልግና የተመላባቸው የንቀት አነጋገሮች የተራው ዜጋ መረን የለቀቁ የመሸታ ቤት ቀልዶች ወይም መዘራጠጦች አይደሉም፤ የቱባ ቱባ የድርጅቱ መሪዎች እምነቶችና አመለካከቶች ናቸው። ድርጅቱ ደግሞ የሚመራው እንዲህ ዓይነት የዘቀጠ አሳፋሪና ኋላ ቀር አመለካከት የሚያመነጭ አእምሮ በተሸከሙና እንዲህ ዓይነት አቋም በሚያራምዱ




ካርታ ቁ. 4፥ የትግራይና ተዋ ሳኝ ክፍለ-ሃገራት ካርታ ቅድመ 1983 ።

ፋሺስቶች ነው። የተሓህት/ወያነ መሪዎች እንዲህ ዓይነት አመለካከት አንግበው ደግሞ እንዲህ ከሚንቁትና ከሚጠሉት ሕዝብ ጋር የሚያቆራኛቸውን ታላቅ ትግራይ ለመመስረት የሚነሱበት አሳማኝ ምክንያት የለም፤ እስስትን የሚያስንቀው ተለዋዋጭ ባህሪያቸው እንዳለ ሆኖ።

ካርታ ቁጥር 4 ተሓህት/ወያነ ሥልጣን ከመቆጣጠሩ በፊት የነበረው የትግራይ እና ተጐራባች ክፍለ-ሀገሮች ክልል የሚያመለክት ሲሆን ከዚህ በታች የሚታየው ካርታ ቁጥር 5 ደግሞ ድርጅቱ የመንግሥትን ሥልጣን ወሮ ከያዘ በኋላ ያወጣው ነው። ካርታ ቁጥር 5 ድርጅቱ መጀመሪያ ቀርፆዓቸው ከነበሩት ሁለት ካርታዎች ፈጽሞ የተለየ ነው (በክፍል ፣ ውስጥ እና ወረድ ብሎም በአባሪነት ከቀረቡት ካርታ

ቁጥር 1 እና ቁጥር 2 ጋር ያነጻጽሩ)። እንዲህ ዓይነቱ መገለባበጥ አንድም የድርጅቱን የመነሻና የመድረሻ አቋምና አምክንዮ አልባነት፣ አለያም ወንዝ በተሻገረ ቁጥር የሚጠቀምበት ተራ የማጭበርበር ዘዴ ከመሆን አልፎ ሌላ ምንም ነገር ሊሆን አይችልም። ተሓህት/ወያነ ሲመሠረት ፀረ-አማራ ጠባብ ብሄርተኛ ድርጅት፣ ሰንበት ብሎ ደግሞ የብሄር-ብሄረሰቦች መብት የተከበረባት ኢትዮጵያ እውን ለማድርግ የሚታገል አገራዊ ኃይል፤ አንዴ በማርክሳዊ-ሌኒናው ርዕዮተ-ዓለም የሚመራና ዓለም-አቀፋዊ ራዕይ ያለው (እሱ ነኝ እንደሚለው የትግራይ ብሄረተኘቱን ሳይለቅ) የዓለም የላብ አደሮች ትግል አካል፣ ከረምረም ብሎ ደግሞ የካፒታሊስት ሥርዓት አራማጅና የሥርዓቱ አፍሪካዊ ደቀ-መዝሙር፣ ሌላም ሌላም መሆኑን ላስተዋለ ይህ ድርጅት ከአየር ባየር ተራ የፖለቲካ አጭበርባሪነትና አቋም የለሽነት በቀር ሌላ ባህርይ ሊያይበት አይችልም። ተወደደም ተጠላም ተሓህት/ወያነ ከውልደቱ ጀምሮ ያልቀየረው አላማ ቢኖር ኤርትራ የተባለችን አገር መፍጠርና ጥቅሟን ማስጠበቅ ብቻ ነው።


ተሓህት/ወያነ አገሪቱን ከመቆጣጠሩ በፊትና ከተቆጣጠረ በኋላ ያሉት ካርታዎች (ካርታ ቁጥር 4 እና 5)




ካርታ ቁ. 5፥ ድኅረ - 1983 የትግራይና ተዋሳኝ ክፍለ-ሃገራት ካርታ።

አንድ ላይ ተጣምረው ሲነጻጸሩ ተሓህት/ወያነ ምንን ከማንና ከየት ወስዶ ለማንና በየት በኩልስ እንደጨመረ በግልጽ ለመረዳት ይቻላል። ድርጅቱ በከበሮ አሳጅቦ የሚለፍፈውን ሳይሆን የሚያደርገውን ለማየትና ለማወቅ ለሚፍልጉ ይህ ተግባሩ ቢያንስ ቢያንስ የድርጅቱ አድላዊነት ለማን እንደሆነ ለመገንዘብና ዓላማውን ለማወቅ የሚያስችል መነጻር ነው (ካርታ ቁጥር 6 ይመልከቱ)።

ከዚህ በታች በካርታ ቁጥር 6 ለማመልከት እንደተሞከረው በቁጥርና ፊደል ከተመለከቱት የትግራይ



ካርታ ቁ. 6 ፥ የአሁኗ እና የቀድሞዋ ትግራይ ካርታ።

1 ከጐንደር ተወስዶ በትግራይ የተጠቃለለ አካባቢ

2 ከወሎ ተወስዶ በትግራይ የተጠቃለለ አካባቢ

3ሀ ለአፋር ተቆርጦ ከተሰጠው የተረፈ የዓጋመ አውራጃ ክልል

3ለ ከዓጋመ አውራጃ ተወስዶ ለአፋር የተሰጠ ክልል

4ሀ ለአፋር ተቆርጦ ከተሰጠው የተረፈ የኽልተ-አውላዕሎ አውራጃ ክልል

4ለ ከኽልተ-ኣውላዕሎ አውራጃ ተወስዶ ለአፋር የተሰጠ ክልል

5ሀ ለአፋር ተቆርጦ ከተሰጠው የተረፈ የእንደርታ አውራጃ ክልል

5ለ ከእንደርታ አውራጃ ተወስዶ ለአፋር የተሰጠ ክልል

6ሀ ለአፋር ተቆርጦ ከተሰጠው የተረፈ የራያና አዘቦ አውራጃ ክልል

6ለ ከራያና አዘቦ አውራጃ ተወስዶ ለአፋር የተሰጠ ክልል

የትግራይና የኤርትራ ወሰን

የቀድሞ የትግራይ ወሰን ከወሎና ከጐንደር ጋር

አዲሱ የትግራይ ወሰን ከወሎና ከጐንደር ጋር

ተሓህት/ወያኔ ያሰመረው የአሁኗ ትግራይና አዲስ የፈጠረው የአፋር ክልል ወሰን

አውራጃዎች ቆርጦ ወደ አፋር ክልል ያካተተው በካርታው ላይ የተመለከቱት አውራጃዎች የቆዳ ስፋት አሁን ቀርቶ ካለው በእጅጉ የበለጠ ነው፤ ከዓጋም አውራጃ በቀር። ትክክለኛ ግምቱን ለካርታ ባለሞያዎች ትቶ የዓይን ግምት ቢሰጥ ከድሮዋ ትግራይ ግማሽ (50 %) ያህሉን ነው ተሓህት/ወያነ ወደ አፋር ክልል የሰደደው። ይህ የተደረገው ደግሞ ከዓድዋ፣ አክሱምና ሽሬ ሳይሆን ከዓጋመ፣ ከኽልተ-

ኣውላዕሎ፣ ከእንደርታና ከራያና አዘቦ ነው። ከፊል ተምቤንን ጨምር እነዚህ አውራጃዎች ደግሞ ድርጅቱ በኢድኅ፣ በኢሕኣፓና በደርግ ደጋፊነት፤ ለትግሉ ምንም ወይም የረባ አስተዋፅዖ ባለማድረግ፣ በፀረ-ኤርትራነትና በመሳሰሉት ሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ቂም ቋጥሮባቸው የኖሩ አካባቢዎች ናቸው።

## ማጠቃለያ

እላይ ለማመልከት እንደተሞከረው የትሓህት/ወያነና የትግራይ ሕዝብ ዓላማ ሆድና ጀርባ ነው። የትግራይ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት ጐልቶ በሚታይ ደርጃ ይህንን ፋሺስታዊ መንደርተኛ ቡድንን ሲቃወም አለመታየቱ በገሃድ የሚታይ ነገር ነው። ይህ ግን የትግራይን ሕዝብ ብቻ የሚመለከት ጉዳይ አይደለም። አፋሩን፣ ጉራጌውን፣ ኦሮሞውን፣ ሶማሌውን፣ አማራውን፣ ቤንሻንጉሉን፣ ... በአጠቃላይ መላውን የአገሪቱን ሕዝብ የሚመለከት ነው። ከዚህ በላይ ደግሞ ይህ ጐሳ-በቀል ፋሺስታዊ አገዛዝ (Ethno-fascist regime) ትግራይን ነጥሎና ከርችሞ ዘግቶ ከሌሎች ክፍሎች በተለያ ሁኔታ የሚገዛበት ሥርዓት ፈጥሯል።

የትግራይ ሕዝብ በተሓህት/ወያነ፣ በሕዝብ ደኅንነት፣ በገበሬዎች ማኅበር፣ በወጣቶች ማኅበር፣ በሴቶች ማኅበር፣ በአካባቢ ህዝባዊ ሠራዊቶች፣ ከድርጅቱ ጦር በተቀነሱ ታጋይ-ነበሮችና በሌሎች መሰል መዋቅሮች እጅ-ተወርች ተቀፍድዶ ያለ ሕዝብ ነው። አገዛዙ ኢትዮጵያን በእስካሁን ታሪክዋ ዓይታው በማታውቅ የደኅንነት መዋቅርና (አንድ ለአምስትን አደረጃጀትን ልብ ይሉዋል) የመረጃ ሠራዊት ተብትቦ በመንፈሳዊ ሽብር አሽማቅቆ እየገዛ ያለ ለመሆኑ እሙን ቢሆንም የትግራይ ሁኔታ ግን ከዚህ እጅግ በጣም የከፋና የጠጠረ ነው። እንኳንስ በአገር ውስጥ በውጭ አገርም በተለያዩ ስብስቦች ለመተብተብ ድርጅቱ የሚሠራው ሥራና የዘረጋው መዋቅር ቀላል አይደለም።

የትግራይ ተወላጆች እንደሌላው በንግድ ፈቃድ፣ በቤት ምሪትና በኮንደምንየም ዕደላ እየተሸነገሉ ሳይሆን አንድም ከሀዲ ትግሬ ተሰኝቶ ላለመነጠል ብለው ነው በድርጅቱ ዙርያ የተኰለኰሉት። ከዚያ ካለፈ ደግሞ እኛ ከሌለንና ከእኛ ጋር ካልወገንክ አማሮችና ነፍጠኞች ያጠፉሃል በሚል መንፈሳዊ ሽብር ተቀፍድደው ነው ከድርጅቱ ጐን የሚኰለኰሉት። ከዚህ በላይ ደግሞ የድርጅቱ የግል ንብረት ተደርጐ ስለ ተሸነሸነ ማንም የክልሉ ተወላጅ ተሓህት/ወያነ እንዲያስብ ከሚፈልገው ውጭ እንዲያስብ እንኳን አይፈቀድለትም። ትግራይ ውስጥ የክፍለ-ሀገሩ ተወላጅም ቢሆን ከድርጅቱ ሌላ ዝር እንዳይል ተደርጐ የተሸነሸነ በመሆኑ ትላንት አብርዋቸው በቆሰሉና በደሙ የትላንት ጓዶቻቸው የተለየ አመለካከት ስለያዙ ብቻ የሚፈጽሙባቸው አረመኔያዊ ተግባር መመልከቱ ይበቃል። ይህ ማመን የሚከብዳቸው ካሉ የችግሩን ሀሁ መገንዘብ እንዳልቻሉ መረዳት ይገባቸዋል።

ምንም እንኳን አብላጫው የየትኛውም የትግራይ ክፍል ሕዝብ የተሓህት/ወያነን ዓላማ የማይደግፍ ቢሆንም አገዛዙ በሚያካሂድበት የስነ-ልቦና ዘመቻ ወዳጁንና ጠላቱን በመለየት ረገድ ብዥታ የለበትም ማለት ግን አይደለም። አገዛዙ ጐሳን ማእከል ባደረገ የግዛት ክፍፍልና ከፋፍለህ ግዛ ዘዴ በመጠቀም በሕዝቡ መካካል የመፈራራትን ንቃቃት ለመፍጠር ያደረገው ጥረት ቀላል አይደለም። እኛ ከሌለን አማሮች፣ ነፍጠኞች፣ የድሮው ሥርዓት ናፋቂዎች፣ የደርግ ርዝራዦች፣ ሻዕቢያ፣ ኦነግ፣ ወዘተ ... ያጠፉሃል የሚለው ፕሮፓጋንዳ ዝም ብሎ አሸዋ ላይ እየፈሰሰ ነው ብሎ ማሰብ አስፈሪ ድንቁርና ነው። ይህ ጥረት ደግሞ የፈጠረው አደጋ የለም ማለት አይቻለም። በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን ጐሳዊ አመለካከት እንዲነሳሳና አጥንትና ሥጋ እንዲለብስ እየበቃ ነው። በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ የተሰገሰጉ አንዳንድ ዋልጌዎችና የአገዛዙ ስውር መለእክተኞች የሚያሰሙት በትግራይ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረ ዛቻና ማቅራራትም በአገዛዙ አፈቀላጤዎችና በየአዋቂ አጥፊ ድርጐኞቻቸው እየተጋነነ ለዚህ ማረጋጋጫና አቀጣጣይ ነዳጅ ሆኖ እያገለገለ ነው። የተቃዋሚው ጐራ ከእንደዚህ ዓይነት መተከላዊና ስልታዊ (strategic and tactical) ስህተት የጸዳ መሆን ይገባዋል።

እላይ ለማብራራት እንደተሞከረው የትግራይ ሕዝብ ወዲህ፤ ተሓህት/ወያነና ሻዕቢያ ከነግሳንግስ ኹርኹሮቻቸው ደግሞ ወዲያ መሆናቸው ተገቢው ግንዛቤ አግኝቶ ሕዝቡን በዕኩልነት የተመለከተና በሙሉ ቅንነትና ኢትዮጵያዊ ፍቅር የሚያይ፣ ታጋሽነት የተመላበት አቋምና የትግል ስልት መከተል የዴሞክራሲያዊ ኃይሉ ይዋል ይደር የማይባል ሥራ ነው። ይህ ደግሞ የዴሞክራሲያዊ ትግሉ ዓቢይ ጥያቄ እንጂ የትግራይንም ሆነ የሌላውን የአገራችን ሕዝብ በተናጠል የሚመለከት ጉዳይ አይደለም። ስለዚህም ነው ዴሞክራሲያዊ የተቃዋሚ ኃይሉ ቆምና ሰከን ብሎ ወዳጅና ጠላትን በቅጡ መለዬት ዋነኛውና ቀዳሚው ግዴታው የሚሆነው። መላውን የአገሪቱ ሕዝብም ይህንን ጉዳይ በሚገባ ማየት እንዲችል ለማብቃት በብቃት መሥራት ያለበት። የሚሰምር ትግል ለማካሄድ ከማን ጋር ተጎዳኝቶ ማንን መታገል እንደሚገባ፤ ማን ጊዜያዊ ወዳጅ፣ ማንስ የዘለቄታ አጋር እንደሆነ መለየት የትግሉ ሀሁ ነው። ወዳጅንና ጠላትን አብጠርጥሮ ማወቅ ለትግሉ ስኬት ወሳኝ አስተዋጾ አለው። እነ ከህደቱን የመሳሰሉ ለወያነ ያደሩ ወይም፤ ቢያንስ ቢያንስ የማይጎረብጡት መጫኛዎች፤ መገለል ያለባቸው መዥገሮች ናቸው ሲባሉ አልሰማ ያሉት የከፈሉት ዋጋና በትግሉ ያደረሱት ጉዳት ለአፍታም ቢሆን ሊዘነጋ አይገባም።


ከዚህ እሳቤ በመነሳት የሚከተሉትን ጥቂት ጥያቄዎች አንስቶ ተገቢ መልስ መስጠት ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ። የትግሉ ዓላማ ምንድነው? ጠላት ማን ነው፣ ለምንስ በጠላትነት ተፈረጀ? በትግሉ ውስጥ ተሳታፊ ነን የሚሉት ወገኖች እነማን ናቸው? ታጋይ ነን ከሚሉቱ ውስጥ ከጠላት ዓላማ ጋር የሚቃረን ግልጽ ዓላማ ያላቸው እነማን ናቸው? የፖለቲካ ሥራ-አጦችና ቀላዋጮች፣ የግል ዝና አስዳጆች? ጠጠር ያለ ነገር ሲያጋጥም ሸብረክ የሚሉ ልፍስፍሶች የሆኑትስ እነማን ናቸው? የሕዝቡ ዝግጁነትስ ምን ያህል ነው? ለምንስ ነው ሕዝቡ ታጋይ ነኝ ላለ ሁሉ ልቡን የሚሰጠው? እንደነዚህ የመሳሰሉ መሠረታዊ

ጥያቄዎች ተገቢው መልስ ባላገኙበት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ወደፊት ለመጓዝ መጣር አውድማ ማስኬድ ነው። የአውድማ በሬ መንዳት ነው።

ከትግል ስልትና ወዳጅና ጠላት ከመለየቱ ሥራ ጋር ተዛምዶ ሊነሳ የሚችል ሌላ አንድ በጣም ወቅታዊ የሆነ ጥያቄ አለ፤ ለምንድን ነው የሆነ የፖለቲካ አጀንዳ ይዞ የሚታገል ድርጅት እያለ የተቀዳ እስኪመስል ድረስ ተመሳሳይ የሆነ መርሃ-ግብር ነድፎ ብቅ የሚል አዲስ ድርጅት የሚያስፈልገው? ከመብት ጥያቄ አኳያ ይህንን ማድረግ በመሠረቱ ስህተት ባይሆንም አገራችን በምትገኝበት የክፍፍል አደጋ ውስጥ ተሆኖ ግን ቅንጦት ብቻ ሳይሆን በእሳት መጫወት ነው። እየዬ ሲደላ ነውና ቢቆየንስ?!


የአንድነት ትግሉ በርትቶ አገራችንን ከብተና እንድንታደግና ፍትሃዊ ሥርዓት እንዲነግሥ ግቢያችንን አጽድተን ተቃቅፈን እንራመድ።

## <u>አባሪ ካርታዎች (ከክፍል 1)</u>



ካርታ ቁ. 2

ከ*People's Voice. Publication of the Tigray People's Liberation Front, Vol. 12, No. 1 & 2. January – June 1990* የተወሰደ ነው።




• Location. Tigray is situated in the northern part of Ethiopia. On the north and east, it is bounded by Eritrea; on the south by Wello and southwest by Gondor regions; and on the west by Sudan

## ዋቢ


ገብሩ አሥራት (2006)፣ ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ፣ Gaithersburg [Maryland]: Signature Book Printing.

Aregawi Berhe (2009). *A Political History Of The Tigray People's Liberation Front (1975-1991)*. Los Angeles [CA]: Tsehai Publishers.

Gebru Tareke (2009). *The Ethiopian revolution: war in the Horn of Africa*. New Haven, [Conn.]: Yale University Press.

Jenny Hammond (1999). *Fire from the Ashes: A Chronicle of the Revolution in Tigray, Ethiopia, 1975-1991*. Asmara: The Red Sea Press, Inc.


ክፍል 3 ይቀጥላል በተዛማጅ ጉዳዮች ላይ።